# የኢትዮጵያውያን ማህበር በሆላንድ
# Vereniging van Ethiopiërs in Nederland
# Ethiopian community in The Netherland

*ቀን፦ 12-11.2013*

Den Haag




## የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪ

ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ከሁሉ አስቀድመን ሠላምና ጤንነትን ከልብ እንመኝላችዋለን።
አይቻልም እንጂ ቢቻል፣ ማንም ይሁን ምን የሠው ፍጡር የሆነ ሁሉ አይቸገር። የችግሩ አይነትና መጠን ሊለያይ ይችል ይሆናል እንጂ ችግር ጨካኝ ነው። ምንጊዜም ማንንም አይፈራም። ጊዜውን ጠብቆ በሁሉም ላይ ይደርሳል።
ነገር ግን ችግር፣ የችግሮች ሁሉ አውራና ከባድ የሚሆነው፣ በድህነት ወይም በማጣት ላይ ሠላምና ተሥፋ ማጣት ሲጨመርበት ነው። ተስፋ ማጣት ወይም ተስፋ መቁረጥ ከሞት የከፋ ነው። አማራጭ ያሳጣል።

ውድ የሀገራችን ዜጎች በሐገራችን ባለው ከፋፋይ፣ አፋኝ ፣ ደካማና ብልሹ አስተዳድር የተነሳ፣ እንደልባቸው ሥራ ሠርተው ኑርዋቸውን ለማሻሻልና በነጻነት ለመኖር ባለመቻላቸው ተስፋ በመቁረጥ፣ ከሚወዱት ቤተሰብና ከወዳጅ ዘመድ ርቀው በመስሰደድ፣ በባዕድ ሀገር በተደጋጋሚ ለእጅግ አሳዛኝና አሰቃቂ እልቂት ከመዳረጋቸውም በላይ በሕይወት ያሉትም ቢሆኑ በብዛት የቁም ፍዳቸውን እያዩ ይገኛሉ።
በተለይም በአብዛኛው ወደ የአረብ ሐገሮች በሚሄዱት ወገኖቻችን ላይ፣ ዘርና ቀለም ሳይለኝ ሠባዊነት ለሚሠማውና እምነት ወይም ፈርሃ እግዚአብሔር ላለው የስው ፍጡር ሁሉ፣ ለመስማት የሚዘገንን። ለማየት የሚቀፍ።
ለመንገር የሚያሳፍር። መርዶና የግፍ ግፍ እየሠማንና እያየን መኖር ከጀመርን እንሆ ከ20 ዓመታት በላይ ሆነን።
ይህን የመሰለውን ውርደትና ጥቃት ሁልጊዜ መስማትና ማስተናገድ የተለማመድነው ወይም አሜን ብለን የተቀበለው እስኪ መስልብን ድረስ፣ የተደረገውንና የሚሆነውን ሁሉ እየሠማንና እያየን አብዛኞቻችን ዝምታን መርጠናል።
ይህም ድርጊታችን ከቶውንም ሊያሳፍረንና ሊጸጽጸተን ይገባል።
በመሰረቱ ይህን የዜግነት መብቱን የሚያስከብርለት መንግስትና አይዞህ ባይ የሌለውን ምስኪን ትውልድ፣ ቢያንስ በዚህ በሰለጠነው ዓለም ያለን ወገኖቹ፣ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን፣ ምንጊዜም አቤት ልንልለትና ልንጮህለት ይገባል። የሞራልና የዜግነት ግዴታም አለብን። ይህ ውርደት በዘላቂነት የሚያጠቃውና አብሮን የሚኖረው እኛን በሕይወት የምንኖረውን እንጂ የሞቱትን እንዳልሆነ ልናጤነው ይገባል። እስከመቼ ድረስስ በደልና ጥቃትን ብቻ አስተናጋጅ ሆነን እንዘልቀዋለን?

ሰሞኑን የእስልምና እምነት መዲና በሆነችው በሳውዲ አረብያ፣ በሚኖሩ ውድ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ላይ እጅግ ከፍተኛ ጥቃት እየደረሰባቸው መሆኑ የዓለም መገናኛ ብዙሀንን ያጣበበ ዜና ሁንዋል።
ውድ እህቶቻችን በማያውቁት ሐገር፣እጅግ አነስተኛ ለሆነ ገቢ በባርነት መኖራቸው ሳያንስ፣ ክቡር የሆነውን ውድ ሕይወታቸውንና አዕምሮቸውን እያጡ ነው።
ከሰው እንዳልተፈጠሩ ሁሉ ዛሬ የእንስሳት መበት ሣይቀር በሚከበርበት በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሰብዓዊ መብታቸው በገሀድ (በጠራራ ጸሀይ) እጅግ በጣም በአስቀኛሚ ሁኔታ እየተጣሠ ይገኛል።
በሳውዲ የወያኔ ኢሕአዴግ መንግስት ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ጽ/ቤት ምንም ጥረት ባለማድረጋቸው ወይም ለማድረግ ባለመፈለጋቸው በደሉ እጅግ ተባብሰዋል።

AnnaSpengelerstraat 75, 1054 NH Amsterdam , Postbus 25763, 2502 HT 'S- Gravenhage

*በመሠረቱ ሊሆን የሚገባው የነበረው ይህን መከራውን እያየ የውጭ ምንዛሪ በነጻ ወደ ህገር ውስጥ በገፍ የሚያስገባለትን ኃይል፣ ሌላው ቢቀር ለዚህ ጥቅሙ ሲል ብቻ ባግባቡ መንከባከብና መብቱን ሊያስከብርለት በተገባ ነበር። ድርጊቱ ግን በየጊዜው የዚህ ተቃራኒ ነው።*
*በዚህም ምክንያት የዜግነት መብታቸውን የሚያስከብር መንግስት ባለመኖሩ አቤት ባይ አጥተዋል። ለመሆኑ ይህን መንግስት የምንደግፍ ወገኖች ለዚህ አሳፋሪ ድርጊቱ ምላሻችን ምን ይሆን?*
*ተቆርቅዋሪ መንግስትና ባለቤት የሌለው ሕዝም እንደሆነ በውል የተገነዘበው የሳውዲ አረቢያ እስላማዊ መንግስት ወደ ግዛቱ ውስጥ በሚገቡ በሠላማዊ ውድ ወገኖቻችን ላይ በየጊዜው ከፍተኛ የሠብአዊ መብት መጣስወንጀል በማድረስ ላይ ይገኛል። ይህን አይን ያወጣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ለማስቆምና ዜጎቻችን ሰብዕናቸው ተጠብቆ፣ ለደረሰባቸው ጥቃት ካሳ ተከፍሎቸው በክብር ወደ ትውልድ ሐገራቸው በሠላም እንዲመለሱና ወንጀለኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ ድምጻችንን ለማሰማት ሰላማዊ ሰልፍ ጠርተናል።*
*የሐገር ልጅ ጥቃት እንደራሳችሁ የሚሰማችሁ በሆላንድ ውስጥ የምትኖሩ ወንድሞችና እህቶች በሙሉ ያልሰሙትን በማሰማት አብረን ድምጻችንን እንድናሰማ ጥሪያችንን እናቀርባለን።*

**ቦታ በሆላንድ የሳውዲ አረቢያ ኤምባሲ (Embassy of Saudi Arabia in The Netherlands), Alexander Street 19, Postcode 2514JM, The Hague ሲሆን መሰባሰቢያና መነሻ ቦታ ደንህግ ዋናው ባቡር ጣቢያ (Central station) ፊት ለፊት ማሊቬልድ (malieveld) ነው።**
**ቀን 18.11.2013**
**ሰዓት ከ1000- 1400**

*ከአክብሮት ሰላምታ ጋር*

*የኢትዮጵያውያን ማህበር በሆላንድ*










AnnaSpengelerstraat 75, 1054 NH Amsterdam , Postbus 25763, 2502 HT 'S- Gravenhage
Tel.03120-6180694/0652642259 , Email:info.venholland@gmail.com , INGbank Nr. 5487444 , **KvK Nummer. 55481345**



ይህ አብዙ በጥቂቱ ነው።

AnnaSpengelerstraat 75, 1054 NH Amsterdam , Postbus 25763, 2502 HT 'S- Gravenhage
Tel.03120-6180694/0652642259 , Email:info.venholland@gmail.com , INGbank Nr. 5487444 , **KvK Nummer. 55481345**







AnnaSpengelerstraat 75, 1054 NH Amsterdam , Postbus 25763, 2502 HT 'S- Gravenhage
Tel.03120-6180694/0652642259 , Email:info.venholland@gmail.com , INGbank Nr. 5487444 , **KvK Nummer. 55481345**




http://www.ethiotube.net/video/28201/Warning-Gross-human-rights-violations-against-Ethiopian-immigrants-in-Saudi-Arabia--November-2013

ቀደም ብለው ይህን ቢዲዮ ካላዩ ይመልከቱት




*የችግሩ አይነትና መጠን ሊለያይ ይችል ይሆናል እንጂ ችግር ጨካኝ ነው። ምንጊዜም ማንንም አይፈራም። ጊዜውን ጠብቆ በሁሉም ላይ ይደርሳል።*

AnnaSpengelerstraat 75, 1054 NH Amsterdam , Postbus 25763, 2502 HT 'S- Gravenhage
Tel.03120-6180694/0652642259 , Email:info.venholland@gmail.com , INGbank Nr. 5487444 , **KvK Nummer. 55481345**